# አምላክ የሚቀበለው አምልኮ (ክፍል 1)

ይህ ትምህርት የተመሠረተው ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው? በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ 15 ላይ ሲሆን መጽሐፉ jw.org/am ላይ ይገኛል።

**ዓላማው፦ ምን ብለህ እንደምታምንና እንዲህ ያለ እምነት ልታዳብር የቻልክበትን ምክንያት ፈትሽህ ለማወቅ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምርና እምነትህን ለሌሎች ማስረዳት የምትችለው እንዴት እንደሆነ ለመመርመር።**



## ሁሉም ሃይማኖቶች በአምላክ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው?

### 1 እምነትህን ፈትሽ

አንዳንድ ሰዎች ‘ተቀባይነት አላቸው’ የሚል መልስ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

አንዳንድ ሰዎች ‘ተቀባይነት የላቸውም’ የሚል መልስ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

አንተስ ምን ብለህ ታምናለህ?

________________________________________

እንዲህ ብለህ እንድታምን ያደረገህ ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 2 መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር መርምር

### አምላክን እሱ በሚፈልገው መንገድ ማምለክ አለብን።
(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 15 አንቀጽ 1-4 ተመልከት።)

**ማቴዎስ 7:21-23ን አንብብ።**

ኢየሱስ በተናገረው ሐሳብ መሠረት በኢየሱስ ወይም በአባቱ እናምናለን ብሎ መናገር ብቻ በቂ ያልሆነው ለምንድን ነው?

**ማቴዎስ 7:13, 14ን አንብብ።**

አብዛኞቹ ሰዎች ትክክለኛውን ሃይማኖት የማይከተሉ መሆናቸው ሊያስገርመን የማይገባው ለምንድን ነው?




**እውነተኛው ገንዘብ ምን እንደሚመስል ካወቅን የሐሰት ገንዘብ የትኛው እንደሆነ መለየት ቀላል ይሆንልናል። በተመሳሳይም እውነተኛውን ሃይማኖት እንዴት መለየት እንደምንችል ካወቅን የሐሰት ሃይማኖቶችን በቀላሉ ለይተን ማወቅ እንችላለን**



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

**እውነተኛውን ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች የሚያስተምሩት ትምህርትና ድርጊታቸው እውነተኛውን ሃይማኖት እንደሚከተሉ ያሳያል።**

(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 15 አንቀጽ 5-14 ተመልከት።)

## መዝሙር 83:18ን፣ ማቴዎስ 20:28ን እና 2 ጢሞቴዎስ 3:16, 17ን አንብብ።

እውነተኛ ክርስቲያኖች አምላክን፣ ኢየሱስንና መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ምን ብለው ያምናሉ?

## ማቴዎስ 24:14ን፣ ማርቆስ 12:17ን እና ዮሐንስ 13:35ን አንብብ።

የአምላክ ሕዝቦች እውነተኛውን ሃይማኖት እንደሚከተሉ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያሳዩት እንዴት ነው?

የይሖዋ ምሥክሮች እውነተኛውን ሃይማኖት እንደያዙ እርግጠኛ ልትሆን የቻልከው ለምንድን ነው?



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 3 እምነትህን ለሌሎች አስረዳ

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**ሁሉም ሃይማኖቶች ጥሩ ነገር አላቸው።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**እርግጥ ሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ጥሩ ሰዎች አሉ። እኔ ግን አምላክ የሚቀበለው አንድ ሃይማኖት ብቻ እንደሆነ አምናለሁ፤ ምክንያቱም . . .**

______________________________

______________________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

______________________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

______________________________

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**እኔ የምከተለው ሃይማኖት ብዙ ተከታዮች አሉት። መቼም ይህን ያህል ብዛት ያለው ሰው ሊሳሳት አይችልም።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**ብዙ ሰዎች በዚህ ሐሳብ ይስማሙ ይሆናል። እኔ ግን የተለየ አመለካከት አለኝ፤ ምክንያቱም . . .**

______________________________

______________________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

______________________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

______________________________



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania